# የተሻሻለ የልዩ ልዩ ጥቅማ-ጥቅም አሰጣጥ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 439/2013

Revised Guidelines for the Implementation of Various Benefits (Directive No. 439/2013)


የገቢዎች ሚኒስቴር
FDRE Refugees and Returnees Service


ጥር 15፥ 2013

# የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ አስተዳደር
# የተሻሻለ የልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅም አሰጣጥ አፈፃፀም
# መመሪያ ቁጥር 439/2013

## መግቢያ

መ/ቤቱ ለሠራተኛው የሚሰጠው የጥቅማ ጥቅም ክፍያዎች በአባላቱ ዘንድ መታወቅ ስለሚኖርበት፣ ለሠራተኛው የሚሰጠው ልዩ ልዩ ጥቅሞች ሁኔታና አኳኋን ተፈፃሚነት ሊኖርው እንደሚችል በግልፅ መቀመጥ ስለሚገባው አስተዳደሩ የሚከተለውን ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅም አሰጣጥ መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

   ይህ መመሪያ «የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ አስተዳደር የተሻሻለ የልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞች ክፍያ አሰጣጥ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 439/2013» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

   የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጥ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. «አስተዳደር» ማለት የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ አስተዳደር ማለት ነው፡፡
2. «የበላይ ኃላፊ» ማለት የአስተዳደሩ ዳይሬክተር እና ም/ዳይሬክተር ናቸው፡፡
3. «UNHCR» ማለት የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽነር ነው፡፡
4. «ቤተሰብ» ማለት የአስተዳደሩ ባልደረባ ሚስት/ባል እና ልጆች ማለት ነው፡፡

3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአስተዳደሩ ሠራተኞች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ደመወዝና ልዩ ልዩ አበሎች

1. ደመወዝ

ሀ/ የአስተዳደር መ/ቤቱ የደመወዝ ስኬል በማስጠት ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

ለ/ በሥራ ላይ የዋለ የደመወዝ ስኬል ቢያንስ በ3 ዓመት አንድ ጊዜ በገበያ ላይ ያለውን የጉልበት ዋጋ፣ የኑሮ ውድነት እና የሌሎች ድርጅቶችን የመክፈል አቅምና ደረጃ እያነፃፀረ የክለሳ ጥናት በማድረግ በማኔጅመንቱ ሲፈቀድለት በስራ ላይ ያውላል፡፡

2. የኃላፊነት አበል

ሀ/ አስተዳደሩ በሚከተለው መልኩ የኃላፊነት አበል በየደረጃው ለሚገኙ የሥራ ኃላፊዎች ይከፍላል፡፡

| የስራ መደብ | የኃላፊነት አበል |
|---|---|
| ዳይሬክተር | 2,000.00 |

| | |
|---|---|
| ም/ዳይሬክተር | 1,800.00 |
| መምሪያ ኃላፊዎች | 1,500.00 |
| ም/መምሪያ ኃላፊዎች | 1,200.00 |
| ዋና ክፍል መሪዎችና ለዞን ኃላፊዎች | 1,000.00 |
| ለዞን ማኔጅመንት አባላት፣ ለካምኘ አስተባባሪዎችና ሀኪሞች | 750.00 |
| ለካምኘ ማኔጅመንት አባላት | 500.00 |

3. የአደጋ ተጋላጭነት

ሀ/ የአስተዳደር መ/ቤቱ በተለያዩ ደረጃዎች ለሚሰሩ ሙያተኞች የአደጋ ተጋላጭነት አበል ይከፍላል፡፡

| የሙያ መግለጫ | የተጋላጭነት አበል |
|---|---|
| ሜዲካል ዶክተር አ/አ የህክምና ቡድን መሪ | 2,000.00 |
| ሜዲካል ዶክተር /የጤናና ኒውትሪሽን ንዑስ ክፍል ኃላፊ አ/አ/ | 1,500.00 |
| ሜዲካል ዶክተር /ካምኘ/ | 2,000.00 |
| ጤና መኮንን /MPH/ አ/አ | 500.00 |
| ጤና መኮንን /MPH/ ዞን | 1,000.00 |
| ነርስ /ዲግሪ/ | 600.00 |
| ፐብሊክ ሄልዝ /ዲግሪ/ | 600.00 |
| ኢንቫይሮመንታል ሄልዝ /ዲግሪ/ | 600.00 |
| እዋላጅ ነርስ /ዲግሪ/ | 800.00 |

| | |
|---|---|
| *እዋላጅ ነርስ /ዲኘሎማ/* | *600.00* |
| *ነርስ /ዲኘሎማ/* | *400.00* |
| *ላብራቶሪ ቴክኒሽያን /ዲግሪ/* | *800.00* |
| *ላብራቶሪ ቴክኒሽያን /ዲኘሎማ/* | *600.00* |
| *ፋርማሲስት /ዲግሪ/* | *800.00* |
| *ፋርማሲስት /ዲኘሎማ/ ካምኘ* | *400.00* |
| *ጤና ረዳት* | *300.00* |
| *ኮንስትራክሽን ኢንጂነር /አድቫንስ ዲኘሎማ/* | *250.00* |
| *የምህንድስና ባለሙያ /BSC Engineer/* | *750.00* |
| *መካኒክ* | *400.00* |

*4. የቤት አበል*

*ሀ/ መ/ቤቱ በዞንና በካምኘ ተመድበው ለሚገኙ ሠራተኞች በጋራ ወይም በግል የሚኖሩበትን ቤት በመገንባት ወይም በመከራየት ያቀርባል፡፡*

*ለ/ በአዲስ አበባ ለሚመደቡ ኃላፊዎችና ሠራተኞች የአስተዳደር መ/ቤቱ የቤት አበል ይከፍላል፡፡*

*ሐ/ በአዲስ አበባ ለሚመደቡ ኃላፊዎችና ሠራተኞች የሚከፈል የቤት አበል እንደ ወቅታዊ ሁኔታው እየታየ ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል፡፡*

*መ/ የአስተዳደሩ በፊደል «ለ» የተመለከተውን የቤት አበል በየደረጃው ለሚገኙ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በየወሩ ይከፍላል፡፡*

| *የስራ መደብ* | *የቤት አበል* |
|---|---|

| | |
|---|---|
| ዳይሬክተር | 12,000.00 |
| ም/ዳይሬክተር | 10,000.00 |
| መምሪያ ኃላፊዎች | 5,000.00 |
| ም/መምሪያ ኃላፊዎች | 4,000.00 |
| ለዋና ክፍል ኃላፊዎች | 3,000.00 |
| ከስራ መደብ ደረጃ 5 እስከ 10 ለተመደቡ ሠራተኞች | 2,000.00 |
| ከስራ መደብ ደረጃ 1 እስከ 4 ለተመደቡ ሠራተኞች | 1,000.00 |

5. ተሽከርካሪና ነዳጅ

ሀ/ የአስተዳደር መ/ቤቱ ዋና ክፍልን ጨምሮ ከዋና ክፍል በላይ ባለው ኃላፊነት ቦታ ለሚመደቡ የሥራ ኃላፊዎች ተሽከርካሪ ይመድባል፡፡

ለ/ ተሽከርካሪ ለተመደበላቸው የሥራ ኃላፊዎች ነዳጅ በየወሩ ይሰጣል፡፡

| የስራ መደብ | የነዳጅ መጠን |
|---|---|
| ዳይሬክተር | 400 ሊትር |
| ም/ዳይሬክተር | 350 ሊትር |
| መምሪያ ኃላፊዎች | 300 ሊትር |
| ም/መምሪያ ኃላፊዎች | 250 ሊትር |
| ዋና ክፍል ኃላፊዎች | 200 ሊትር |

6. የቴሌፎን አበል

ሀ/ ለዳይሬክተር፣ ለም/ዳይሬክተር፣ ለመምሪያ ኃላፊዎች እና ለም/መምሪያ ኃላፊዎች አስተዳደሩ የሞባይል ቴሌፎን ወጪ ይሸፍናል፡፡

ለ/ አስተዳደሩ ሌሎች በየደረጃው ለሚገኙ ኃላፊዎች በየወሩ ለሞባይል ካርድ ይከፍላል፡፡

| የስራ መደብ | የሞባይል ካርድ ገንዘብ መጠን |
|---|---|
| ለዋና ክፍል ኃላፊዎች | 1000.00 |
| ለዞን ኃላፊዎች | 1000.00 |
| ለዞን ማኔጅመንት አባላት | 1000.00 |
| ለካምኘ አስተባባሪዎች | 1000.00 |
| ለመጠለያ ጣቢያ ማኔጅመንት አባላት | 700.00 |

7. ሕክምና

ሀ/ አስተዳደሩ ሠራተኛውን በአገር ውስጥ ወደተዋዋለባቸው የህክምና ተቋሞች በመላክ ሙሉ ወጪ በመሸፈን ያሳክማል፡፡

ለ/ የመ/ቤቱ አባል ቤተሰብ ሲታመም መ/ቤቱ በሚያቋቁመው ክሊኒኮች ብቻ የህክምና እና የመድኃኒት አገልግሎት ይሰጣል፡፡

ሐ/ ማንኛውም የመ/ቤቱ አባል በአገር ውስጥ ህክምና ሊረዳ እንደማይችል ተረጋግጦ፡-

1. ለከፍተኛ ህክምና ከአገር ውጪ መሂድ እንደሚያስፈልግ በህክምና ቦርድ የተሰጠ ማስረጃ ሲያቀርብ፣
2. ማንኛውም የመ/ቤቱ አባል ያጋጠመው የጤና እክል ጊዜ የማይሰጥ፣ ህክምናው በሀገር ውስጥ የሚሰጥ ቢሆንም በውስን ቦታ ብቻ እንደሚገኝ እና በከፍተኛ ጥንቃቄ የሚሰራ እንደሆነ፣ በታካሚው ህይወት ላይ አደጋ ሊያደርስ የሚችል መሆኑን እና የህክምና አገልግሎቱን ለማግኘት ረዥም ጊዜ

መጠበቅ እንደሚያስፈልግ የሚገልፅ የህክምና ማስረጃ መ/ቤቱ ውል ከገባባቸው የግልም ሆነ የመንግስት የህክምና ማዕከላት ማቅረብ ከቻለ እና የአስተዳደሩ የውጭ ህክምና አገልግሎት የውሳኔ ሀሳብ አቅራቢ ኮሚቴ የቀረበው የህክምና ማስረጃ ትክክለኛ መሆኑን አረጋግጦ ለሰው ሀብት ልማትና ንብረት አስተዳደር መምሪያ ወደ ውጪ ሄዶ እንዲታከም የውሳኔ ሀሳብ ሲያቀርብ፤

3. ማንኛውም የመ/ቤቱ አባል ያጋጠሙው የጤና እክል ጊዜ የማይሰጥ፣ ህክምናው በሀገር ውስጥ የሚሰጥ ቢሆንም በውስን ቦታ ብቻ እንደሚገኝ በከፍተኛ ጥንቃቄ የሚሰራ ካልሆነ በታካሚው ህይወት ላይ አደጋ ሊያደርስ የሚችል መሆኑን መ/ቤቱ ውል ከገባባቸው የግል ወይም የመንግስት ሆስፒታሎች እንዲሁም ሌሎች የህክምና ማዕከላት ታካሚው ውጪ ሀገር ሄዶ መታከም እንዳለበት ትእዛዝ ሲሰጥ እና የአስተዳደሩ የውጭ ህክምና አገልግሎት የውሳኔ ሀሳብ አቅራቢ ኮሚቴ ለሰው ሀብት ልማትና ንብረት አስተዳደር መምሪያ ወደ ውጪ ሄዶ እንዲታከም የውሳኔ ሀሳብ ሲያቀርብ፡፡
4. የታካሚው የጤና ችግር መ/ቤቱ ውል ከገባባቸው የህክምና ማዕከላት አገልግሎቱ የማይሰጥ በመሆኑ ለበሽታው አይነት ህክምናውን የሚሰጡ ስፔሻሊስት ሀኪሞች ከሚገኙበት የጤና ተቋም ግለሰቡ በግሉ በመታከም ከአንድ በላይ በሆኑ ሀኪሞች ወደ ውጪ ሄዶ እንዲታከም ማስረጃ ሲያቀርብ እና የአስተዳደሩ የውጪ ህክምና አገልግሎት የውሳኔ ሀሳብ አቅራቢ ኮሚቴ ለሰው ሀብት ልማትና ንብረት አስተዳደር መምሪያ የውሳኔ ሀሳብ ሲያቀርብ፡፡

ለጉዞ የሚያስፈልገው ሙሉ የትራንስፖርት ወጪ እና ደረሰኝ የሚቀርብበት እስከ 250,000.00 /ሁለት መቶ ሃምሣ ሺህ ብር/ ድረስ ያለውን የህክምና ወጪ ለሁለት ጊዜ አስተዳደሩ ይሸፍናል፡፡

መ/ ማንኛውም የመ/ቤቱ አባል የዓይን መነፅር በሀኪም ሲታዘዝለት እስከ ብር 3,000.00 /ሶስት ሺህ ብር/ ድረስ ያለውን ወጪ መ/ቤቱ ይሸፍናል፣ ሆኖም የዓይን መነፅር ፍሬም ወጪ ከ1,000.00 /አንድ ሺህ ብር/ በላይ አይሸፍንም፡፡

ሠ/ ማንኛውም በሀኪም ታዞለት የዓይን መነፅር የተገዛለት የመ/ቤቱ አባል የመነፅር ፍሬም ቅያሪ ጥያቄ ሊያቀርብ የሚችለው ከአራት ዓመት በኋላ ይሆናል፡፡

ረ/ መ/ቤቱ ለአንድ ሠራተኛ የጥርስ ማስተካከል ጋር በተያያዘ በዓመት እስከ ብር 3,000.00 /ሶስት ሺህ ብር/ ይሸፈናል፣ ወጪው ከዚህ አሃዝ በላይ ከሆነ ጉዳዩ ለም/ዳይሬክተር ቀርቦ ሲወሰን ሊሸፈን ይችላል፡፡

ሰ/ ከጆሮ ህክምና ጋር በተያያዘ ለድምጽ መስሚያ የሚያገለግል መሳሪያ የሚያስፈልግ መሆኑ በሀኪም ሲረጋገጥ የሚያስፈልገውን ወጪ በሙሉ አስተዳደሩ ይሸፍናል፡፡

ሸ/ ለመነፅር ግዥ፣ ለጥርስ ተከላ እና ለጆሮ ማዳመጫ ግዥ የሚያስጠይቁ ወጪዎች ቤተሰብን አያካትቱም፡፡

8. ለብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት ክሊኒክ አገልግሎት የሚውል የመድኃኒት ጥያቄ ሲቀርብ የጤናና ኒውትሪሽን ዋና ክፍል ያለውን የመድኃኒት ክምችት መጠን በመመልከት ከሰው ኃይል ልማትና ንብረት አስተዳደር መምሪያ ጋር በመነጋገር ይወሰናል፡፡

9. በብሔራዊ ደህንነት አገልግሎት ስር ለሚገኙ የተለያዩ ዋና መምሪያ ኃላፊዎች የሚቀርቡ የህክምናና የመድኃኒት ግዥ ጥያቄዎች የሚመለከተው የመ/ቤቱ ኃላፊ ጉዳዩን ከሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ጋር በመነጋገር አገልግሎቱን እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞች

1. የውሎ አበል

ሀ/ የውሎ አበል አከፋፈል በደመወዝ ስኬል መሰረት የሚከፈል ሆኖ፡

| የደመወዝ መጠን | የአበል መጠን |
|---|---|
| ከ1,798.00 እስከ 5,000.00 | 450.00 |
| ከ5,001.00 እስከ 10,000.00 | 525.00 |
| ከ10,001.00 እስከ 15,000.00 | 600.00 |
| ከ15,001 እስከ 20,000.00 | 700.00 |
| ከ20,001 እስከ 25,000.00 | 800.00 |
| ከ25,001 እስከ 35,000.00 | 900.00 |
| ከ35,001 እስከ 45,000.00 | 1000.00 |
| ከ45,001.00 በላይ | 1,200.00 |

*አበል ይከፈላል:: ከዚህ በተጨማሪ፡-*

- *የዳይሬክተር እና የምክትል ዳይሬክተር የአልጋ ሂሳብ ወሰን ሳይኖረው በደረሰኝ ይወራረዳል::*
- *መምሪያ ኃላፊዎች እና ም/መምሪያ ኃላፊዎች የአልጋ ክፍያ እስከ 600.00 /ስድስት መቶ ብር/ በደረሰኝ ይወራረዳል::*
- *የዋና ክፍል ኃላፊዎች የአልጋ ክፍያ እስከ 500.00 /አምስት መቶ ብር/ ድረስ በደረሰኝ የሚወራረድ ይከፈላቸዋል::*
- *የዞን እና መጠለያ ጣቢያ አስተባባሪዎች ወደ ዋናው መ/ቤት ለስብሰባ ሲመጡ ብቻ የአልጋ ክፍያ እስከ 600.00 /ስድስት መቶ ብር/ ድረስ በደረሰኝ የሚወራረድ ይከፈላቸዋል::*
- *የዞን እና የመ/ጣቢያ ማኔጅመንት ወደ ዋናው መ/ቤት ለስብሰባ ሲመጡ ብቻ የአልጋ ክፍያ እስከ 500.00 /አምስት መቶ ብር/ ድረስ በደረሰኝ የሚወራረድ ይከፈላቸዋል::*

*ለ/ ማንኛውም ሠራተኛ ከመደበኛ ሥራ ቦታው ከ15 ኪ.ሜትር በላይ በስራ ምክንያት ወደ ሌላ ስፍራ እንዲንቀሳቀስ ሲታዘዝ በዚሁ ምክንያት ለሚያስከትለው ተጨማሪ ወጪ የሚከፈል ክፍያ ነው::*

*ሐ/ ለክፍያው አፈፃፀም ጉዞ ከመጀመሩ በፊት ወይም ሥራ አከናውኖ ከጉዞ ከተመለሰ በኋላ ሊሆን ይችላል::*

*መ/ የውሎ አበል የሚታሰበው በእያንዳንዱ ቀን ሆኖ ከመደበኛ የሥራ ቦታው ተነስቶ ጉዞ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ተመልሶ መደበኛ ሥራ ቦታው የሚደርስበት ቀን ተዳምሮ ነው::*

ሠ/ የውሎ አበል ክፍያ የሚፈፀመው የሠራተኛው የቆይታ ጊዜና የሥራው አስፈላጊነት በሠራተኛው የበላይ ኃላፊ ሲፈቀድና ሲወሰን ነው::

ረ/ የውሎ አበል ክፍያ መጠንን በሚመለከት መ/ቤቱ በየጊዜው እንዲፀና አጥንቶ ሊያሻሽል ይችላል::

ሰ/ የውሎ አበል የሚሰራ ስራ ከ30 ተከታታይ ቀናት ሊበልጥ አይችልም::

ሸ/ ይሁን እንጂ በፊደል «ሰ» የተጠቀሰው የጊዜ መጠን ማራዘም ሲያስፈልግ የስራ ክፍሉ ከሚመለከተው የስራ ኃላፊ ጋር በመነጋገር ተጨማሪ ከ30 ተከታታይ ቀናት ላልበለጠ ገዜ ሊያራዝም ይችላል::

ቀ/ በተጨማሪነት እንዲፈቀድለት የቀረበው ውሎ አበል ተቀባይነት ካጣ ሠራተኛውን በጊዜያዊት ወይም በቋሚነት አዛውሮ ሊያሰራ ይችላል::

2. የዝውውር አበል

ሀ/ አንድ ሰራተኛ በአስተዳደሩ ውሳኔ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ የስራ ቦታ ሲዘዋወር ለራሱና ለቤተሰቡ የሚከፈለውን የትራንስፖርት ሂሳብ አስተዳደሩ ይሸፍናል፤ ሆኖም ለሠራተኛው በማንኛውም ሁኔታ ከ8 ቀናት በላይ የውሎ አበል ክፍያ አይፈፀምም::

ለ/ የተዘዋወረው ሠራተኛ ለእቃ ማጓጓዣ በሚያቀርበው ደረሰኝ መሰረት እስከ 2000.00 /ሁለት ሺህ ብር/ ድረስ በአስተዳደሩ ይሸፈንለታል:: ይሁን እንጂ ይህ የሚሆነው ለስራ ወደ ማዕከል የሚንቀሳቀሱ የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች አለመኖራቸው ሲረጋገጥ ነው::

3. የበረሃ አበል

ሀ/ በማስተባበሪያ ጽ/ቤቶች እና በመጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ በቋሚነት ለተቀጠሩ ሠራተኞች የበረሃ አበል ይከፈላል::

ለ/ በመ/ቤቱ የሚከፈለው የበረሃ አበል የመጠለያ ጣቢያ ጽ/ቤቶች የሚገኙበት አካባቢ የአየር ሁኔታ፣ የተመቻቸ የሥራ ሁኔታን ወ.ዘ.ተ ከግምት በመውሰድ ከዚህ በሚከተለው ሁኔታ በሶስት ደረጃ በተለየው መሰረት ይሆናል፡፡

በ1ኛ ደረጃ

1. የዶሎ ማስ/ጽ/ቤትና በስሩ የሚገኙ መጠለያ ጣቢያዎች፣
2. የጋምቤላ ማስ/ጽ/ቤትና በስሩ የሚገኙ መጠለያ ጣቢያዎች፣
3. በሠመራ ማስ/ጽ/ቤትና በስሩ የሚገኙ መጠለያ ጣቢያዎች በሙሉ፣
4. ኡኩጉና ኛንጋቶም ስ/መ/ጣቢያዎች፡፡

በ2ኛ ደረጃ

1. ሽመልባና ህፃፅ መጠለያ ጣቢያዎች፡፡

በ3ኛ ደረጃ

1. የአሶሳ ማስ/ጽ/ቤትና በስሩ የሚገኙ መጠለያ ጣቢያዎች፣
2. የጅግጅጋ ማስ/ጽ/ቤትና በስሩ የሚገኙ መጠለያ ጣቢያዎች፣
3. የሽሬ ማስ/ጽ/ቤት፣ የማይዓይኒ እና የአዲሃሩሽ መጠለያ ጣቢያዎች፣
4. የኬንያ ስደተኞች የሰፈሩባቸው መጠለያ ጣቢያዎች /ሞያሌ/፣
5. ሚዛን ተፈሪ ላይዘን ቢሮ፡፡

ሐ/ በ1ኛ ደረጃ ለተመደቡ መጠለያ ጣቢያዎች የመሰረታዊ ደመወዝ 50%፣ በ2ኛ ደረጃ ለተመደቡ መጠለያ ጣቢያዎች የመሰረታዊ ደመወዝ 40% እና በ3ኛ ደረጃ ለተመደቡ መጠለያ ጣቢያዎች የመሰረታዋ ደመወዝ 35% የበረሃ አበል ይከፈላል፡፡

መ/ ለበረሃ አበል መጠን በወጣው ደረጃ መሰረት ከ«UNHCR» ጋር በሚደረገው ዓመታዊ የበጀት ድረድር ላይ መጠኑ ሊሻሻል ወይም ባለበት ሊቆይ ይችላል፡፡

ሠ/ አዲስ መጠለያ ጣቢያዎች ሲከፈቱ ከላይ የተዘረዘሩ ሁኔታዎች ታይቶ ደረጃው ይወሰናል፡፡

4. የምግብ አበል

ሀ/ በዞንና መጠለያ ጣቢያዎች ለሚመደቡ ሰራተኞች አስተዳደሩ የምግብ አበል ይከፍላል፡፡

ለ/ የምግብ አበል አከፋፈሉ ዞኖችና መጠለያ ጣቢያዎች የሚገኙባቸው አካባቢዎች የምግብ ፍጆታ አቅርቦት ለሟሟላትና ለኑሮ ያላቸውን አመቺነት ታሳቢ ያደርጋል፡፡

ሐ/ መ/ቤቱ በሁሉም ዞኖችና መጠለያ ጣቢያዎች ለሚመደቡ ሠራተኞች በየወሩ የምግብ አበል ይከፍላል፤ በዶሎ፣ ሰመራ፣ ጋምቤላ እና በስራቸው በሚገኙ ስ/መ/ ጣቢያዎች ላሉ ሠራተኞች በየወሩ ብር 1000.00 /አንድ ሺህ ብር/ ይከፍላል፡፡ በተቀሩት ዞኖችና ስ/መ/ጣቢያዎች ለሚገኙ ሠራተኞች በየወሩ 600.00 /ስድስት መቶ ብር/ ይከፍላል፡፡

5. የስራና የደምብ ልብስ

ሀ/ የሥራ ፀባያቸው ደንብ ልብስ የሚፈቅዱ የሥራ መደቦች ላይ ለተመደቡ ሠራተኞች የሥራና የደንብ ልብስ ጫማ ይሰጣል፡፡

ለ/ የሥራና ደንብ ልብስ የተሰጣቸው ሠራተኞች በሙሉ በድርጅቱ ስራ ላይ ባሉበት ጊዜ ሁሉ ለብሰው የመገኘት ግዴታ አለባቸው፡፡

ሐ/ የደንብ ልብስ የሚቀርበው በአመት ሁለት ጊዜ ይሆናል፡፡ የልብሱ አይነትና ጥራት በየአመቱ የተፈቀደውን በጀት መሠረት በማድረግ ይወሰናል፡፡

6. ኢንሹራንስ

ሀ/ አስተዳደሩ ለሁሉም የመ/ቤቱ አባላት የህይወት እና የአደጋ መድን ሽፋን ይገባል፡፡ አፈፃፀሙን በሚመለከት በየወቅቱ የገበያው ሁኔታ እየተዳሰሰና እየተጠና እንዲስተካከል ይደረጋል፡፡

7. ተቀማጭ ገንዘብ **/Provident Fund/**

የተቀማጭ ገንዘብ /Provident Fund/ ከአስተዳደሩና ከሰራተኛው ደመወዝ እየተቀነሰ የሚዋጣ ሆኖ ሠራተኛው በተለያዩ ምክንያት ከስራው ሲሰናበት ወይም ሠራተኛው ሲጠይቅና በአስተዳደሩ ሲታመንበት ለሠራተኛው የሚከፈል ነው፡፡ ይህ ኘሮቪደንት ፈንድ የሚወሰደው በ3 ወር አንድ ጊዜ ሆኖ ከተቀማጭ 10% በአካውንቱ እንዲቀር ሆኖ ነው፡፡

ለ/ የተቀማጭ ገንዘብ /Provident Fund/ መጠን አስተዳደሩ ከተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽነር ጋር በሚያደርገው ድርድር በሚፈቀድ በጀት የሚወሰን ሲሆን በአሁኑ ወቅት ከአስተዳደሩ 30% ከሠራተኛው 20% በድምሩ የደመወዝ 50% እንዲቆረጥ ይደረጋል፡፡ በየዓመቱ በሚደረግ የበጀት ስምምነት መሰረት ለውጥ ሲኖር ለሰራተኛው ይገለፃል፡፡

8. የአገልግሎት ካሣ

ሀ/ የአስተዳደሩ ሠራተኛ ከስራ ሲለቅ ወይም ሲሰናበት ለእያንዳንዱ በስራ ለቆየበት ዓመት በአንድ ወር ደመወዝ እየታሰበ ይከፈላል፡፡

ለ/ ከላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ መ/ቤቱ በኘሮጀክት መታጠፍና በበጀት እጥረት ምክንያት ከስራ ሲቀነስ፣ እድሜው ለጡረታ ደርሶ ከመ/ቤቱ ሲያሰናብት የሶስት ወር ደመወዝ ለስራ ማፈላለጊያ ይከፍላል፡፡

9. የቀብር ማስፈፀሚያ

የአስተዳደሩ ሰራተኛ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ ቤተሰቦቹ ወደሚገኙበት አካባቢ ቀብር ይፈፀም ዘንድ አስፈላጊውን ማጓጓዣ ያቀርባል ለቀብር ማስፈፀሚያ የሚሆን ብር 10,000.00 /አስር ሺህ ብር/ በቅርብ ቤተሰብ ወጪ ተደርጎ እንዲከፈል ያደርጋል፡፡

10. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ «የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ አስተዳደር የተሻሻለ የልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅም ክፍያ አሰጣጥ አፈፃፀም መመሪያ» በምክትል ዳይሬክተሩ ከተፈረመበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ዘይኑ ጀማል

ም/ዳይሬክተር